# ዜግነት በተግባር ሲበለጽግ

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*ታሕሣሥ 2002 ዓ.ም.*

ዜግነትን የራስነት ወስጥነት መግለጫ ነው፤ የማንነት ማህተም ነው፤ የደም ልዩ ቋንቋ ነው፤ የአጥንት ትውፊተ ህላዊ ነው። የሚስጢር ማህለቅ የተፈጠሮ ወርቃማ እትብት ነው፤ በእኔ ውስጥ እኛነት በእኛነት ውስጥ ደግሞ እኔነት ገደብ ድንበር አልቦሽ የሚንሸራሸርበት ልዩ አልማዛዊ ሁዲድ ነው።

ዜግነት ወደው እና ፈቀድው የሚቀበሉት የመሆኑን ያህል ፍቅሩ ልክ ወቄት ሊወጣለት የማይችል ቅዱስ መንፈስ ነው። ዜግነት ህሊና ያለው ለህሊናው ያደረ ክቡር ሥነ ምግባር ሲሆን ጥልቅ እና ምጥቅ ህያው ደም እና ሥጋ ነፈስ ነው።

የኢትዮጵያዊነት መጠነ ሰፊ ሊቀ ትርጉሙን የሚያበለጽገውም ይህ በውስጣችን ያለ ውስጣችን ውስጡ ያደረገ ልዩ ቀመሩ ቀለሙ ዓዬው ኢትዮጵያዊነት ዜግነታችን ነው። ኢትዮጵያዊነት በቁሙ የሚነበብ የሚተረጎም አይደልም።

የኢትዮጵያዊነት ደማችን ቀለማችን ገጻችን ውስጣችን በሰማያዊ ጥበብ መሰተጋብራዊ ውህደቱ እዮራዊ ከመሆኑ ላይ ነው። ስለ ጨዋነት፤ ስለ ጅግንንት፤ ስለ ሰላም፤ ፈላጊነት፤ ስለ ይሉኝታ፤ ስለ ሰው አክብሮት፤ ስለ ፍቅር፤ ስለ የማድረግ ብቃት፤ ሰለ ቤተስብ አመሰራረት እና አስተዳደር፤ ስለ ጉርብትና፤ ስለ ኃላፊነት፤ ስለ መውጣት፤ ስለ ትህትና፤ ስለ ትእግስት፤ ስለ ደግነት፤ ስለ እርህርህና፤ስለ አምልኮ፤ ስለ ሥልጣኔ፤ ስለ ማህበራዊ ህይወት፤ ስለ አብሮነት፤ ስለ አንድነት፤ ስለ ነፃነት፤ ስለ ቀደምትነት፤ በሁሉም ዘርፍ መቅዘፊያውን ብናሰተካክልው ኢትዮጵያዊነት የተቀመረበትን ንጥረ ነገረ ሚሰጢርን በቅጡ ማመሳጠር ይቻላል …

<u>**ኤትዮጵያዊነት ተነበርክኮ ተለምኖ የሚገኝ እንጂ የሚገፋ ወይንም የሚያገልሉት አይደለም። ሲታደሉት ብቻ የሚገኝ የዜግነት መለያ አሻራችን ብቸኛው ገላጫችን ኢትዮጵያዊነታችን ነው። ተከብረን፣ ታፍረን፣ ታውቀን፣ ተደንቀን፣ ተናፍቀን የኖርነው በኢትዮጵያዊነታችን እንጅ በትናንሽ ሰፈራዊ ወይንም መንደራዊ ስያሚያችን አይደልም። እሰከዛሬም ያኖረን ወደፊትም የምንኖረው በደማቁ ሰንደቃችን በኢትዮጵያዊነታችን ነው።**</u>

ተሳክቶላቸው የሥራውንም ፈቃድ አግኝተው ጤናቸውም ባንጻራዊ ደህና የሆኑ የመላ ዓለምን ወግኖቻቸውን ወክለው ከጣሊያን፣ ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመን፣ ከስዊዲን፣ ከካናዳ ከኖርዌ ከዴንማርክ፣ ከስዊዘርላንድ ከ150-200 የሚደርሱ ወገኖች በአዬር፣ በዬብስ፣ በባህር ተጉዘው ዴንማርክ ኮፐንህገን <u>በሰንደቃቸው ደምቀው በደማቸው ፍጹም ፈልቀው ተገናኙ!</u>

ኢትዮጵያውያን ነፃነታቸውን ይወዳሉ፣ ያፈቅራሉ ለነፃነታቸው ይንሰፈሰፋሉ .... ኢትዮጵያውያን በሐገራቸው ባንዴራ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ስር ተሰባስበው የእናት ሐገራቸውን የማህፀን ደማዊ ዕንባ ይጋራሉ ብሶቷ እንግልቷ ያንገበግባቸዋል!!

ስለሆንም ነው በዛ የሰውን ልጅ እንደ ድንጋይ ያደረገውን የበረዶ ክምር አሸንፈው ሂሮድስ መለስ ዜናዊ 52 የአፍሪካ ሐገሮችን ወክለው መገኘትን በቁርጠኝነት መንፈስ በልህ ያወገዙት በማለት ሳይሆን በሆኖ መቻል ቀመር ለዓለም ሕዝብ የዘመኑ ፓን አፍሪካኒስት ለመሆን ቅዣቱ ያደናበራቸውን ሂሮድስ መለስ በአንድ ድምጽ ከታህሳስ 17 እሰከ ታህሳስ 18 — 2009 በዴንማርክ ዋና ከተማ በኮፐንህገን ያን ሁሉ እንግልት ችለው እና ታግሰው ምንም ነገር ሳይበግራቸው ተልዕኳቸውን በዜግነት ቀለም በተግባር ያበለጸጉት … ወሸኔ ማለፊያ

ጽናታቸው፣ እልሃቸው፣ ቁርጠኝነታቸው መከራን፣ ፈተናን የመቋቋም ብቃታቸውን ሳስበው ይህን ኃይል በቅንነት የሚመራ የሚያደራጅ የሚያስተባብር ወገን ካለ በእውነት ኢትዮጵያዊነት በራሱ የሚዋጋ ለድልም የሚበቃ ሆኖ ነው ያገኘሁት።

ሌላው እያንዳንዱ ተግባር በራሱ ጊዜ መሪ ነበረው። ከስንት ሐገር የተውጣጣ ወገን አዝማች ኑሮት ማዕከላዊ በሆነ አመራር፡ እንደገናም የተለያዩ የዘርፍ አስተዳደር ኖሮት ተልዕኮን በጨዋነት በሥርዓት በመተሳሰብ እና በፍቅር እንዲሁም በአክብሮት በመስጠት እና በመቀበል እረገድ የነበረው ሰንነሰለት ለእኔ አዲስ የተመክሮ አድማስ ማሳ ነበር ማለት እችላልሁ። ልዩ
አርትም ነበረው ህሊናየን ዓይናማ ያደረገ!

የሴቶች ተሳትፎስ ጥናካሬ በጉዞ ላይ ስንቅ አዘጋጅትው በሰላማዊ ስለፉም ሆነ በስብሰባው እንዲሁ ንብ ሆነው ማዬት በአውሮፓ የነበርኩበት ጊዜ እና አሁን ትልቅ እመርታዊ እድገት ነው ያየሁበት። አንድም መስክ እነሱ ያልተሳተፉበት ፈጽሞ አላዬሁም ... ያለ ማጋናን
ከእኩልነት በለጥ ያለ ተግባር ሴቶች ከውነዋል። አዲስ ዘመን ላይ እንዳለንም ተግባርን በተግባር አብሰረዋል። ስለሆነም ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለተገኙት እህቶቼ ሁሉ ያለኝን የላቀ ፍቅር ከአክብሮት ጋር ሳልገልጽ ማለፍ አልሻም ....

እንዲሆም ያ በረዶ ለእኔ የሱባኤ ጊዜ እንደ ነበር ይሰማኛል። ስለሆንም ሄሮድስ መለስ ዜናዊ በ፡አ፡ፍ፡ሪ፡ካ፡ ምድር ምደረበዳ ላይ የተጎለቱ አለት አደረጋቸው። ሌላው ትልቁ ስንቅ ሐገር ውስጥ ያለው ጨለማው፣ መከራው፣ እሰሩ፣ አድሎው፣ ራሃቡ፣ ጥማቱ፣ መገፋቱ፣ መገፍተሩ ባይታወርነቱ የጎመዘዘው ወገናችን ለተስፋው ስንቅ አቀባይ ነበር የዴንማርኩ ሰላማዊ ሰልፍ
መኩሪያዎቹ ድምጹን አሰተጋቡለት ....

ውጪም ለሚኖሩት ቢሆን ስላልቻሉ ብቻ በፀሎት እና በሁሉም መስክ ተግተው ሲያግዙ ለነበሩ ወገኖቻችንም ቢሆን አደራ መወጣት የከበረ ተግባር ነው እላልሁ።

አውሮፓ አቀፉ ስብሰባ ታህስ 17-2009 ምሽት ላይ ሲካሄድ የነበረው ፍቅር ናፈቆትን- የማዳመጥ ልዩ ተሰጥኦ በህይወቴ የማረሳው ገጠመኝ ነበር።

በተረፈ ሰላማዊ ስልፉ ፈተናን ድል ነስቶ በራሱ ጊዜ የራሱን ስልት እና መርሃ ግብር በመንደፍ የተገባውን ያህል ተልዕኮውን አሳክቷል።

የቡድኑን መሪ አቶ አህመድ ዓሊን /ከሲዊዲን/
አስተባባሪ ....
. ሚዲያ - አባይ ሚዲያ ዋና አዘጋጅ/ /ከእንግሊዝ/
. መረጃ ማዕከል - አንበሳውን አቶ ሃሰን /ከዴንማርክ/
. መሰተንገዶ - ወ/ት ማራኪን /ከሲዊዲን/
. ፕሮግራም መሪ - አቶ 5 ኪሎን /ከከዴንማርከ/
. የሙዚቃ ቅንብር በመሳሪያ-ለስብሰባው - ኢትዮ ካዛንችስ /ከሲዊዲን/
. ስርቢስ - አቶ አባጃሌ፣ አቶ ፍቅሩ፣ አቶ ግሪን አብስንያን፣ አቶ ከሳ /ከዴንማርከ/
ከልቤ ከአክብሮት ጋር አመስገናለሁ።

የቀረ ነገር፡ ቃለ ምልልስ ያደረጉ ወገኖቼ በፈቃዳቸው ለሐገር ውስጥ እና ለውጪ ሚዲያ የሰጡትን፡ እንዲሁም እንደዛ በማያቋርጥ ኃይል መፈክር ሲያሰሙ የነበሩትን መሪዎች ወንድሞቼን እና አንዲት ድንቅ ብርቅዬ እህቴንም፤ የዬሐገሮችን የቡድን፡መሪዎችንም ሰልፈኞችንም ጨምሮ እግዚአብሔር አምላክ ይጠብቅልን እላልሁ፤

አሰተናጋጆቻችን የዴንማርክ አንበሶች ጥራትን በተግባር አሳይተውናል። በመሆኑ ብዙ አስተምረውናል። በምንችለው ሁሉ ልናግዛቸው ይገባል። ተከታታይ ተግባራት ይከውኑ ዘንድም ከጎናቸው እንሰለፍ ... አመሰግናለሁ።

# እንጽና!